# ያልተዘጋ ዶሴ

ከብርሃነሥላሤ ተፈራ

ግልጽ ደብዳቤ፤ ይድረስ ለፀሐፊው

ሚያዚያ 24 ቀን 2000 ዓ/ም (ሜይ 2 ቀን 2008) በአለም አቀፍ የመረጃ መረብ ታዛ ጠለል፤ በጀግኖቹ የኢትዮጵያውያን የመረጃ አውታሮች ሰሌዳ ላይ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር (ፕሬዚደንት) የሆኑትን ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን ለማግኘት የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅመው ብዙ መድከምዎን የሚያበስረው ደብዳቤዎ ሃገር ወዳዱን ዜጋ ሲያነጋግር ሰንብቷል። ሆኖም ከፈላጊውም ይሁን ከተፈላጊው ወገን ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶ መቋጫ ሳይበጅ ቀናትም ተቆጠሩ፤ በአፋልጉኝ ዳባ የተጀቦነውን ይህን የአደባባይ ዶሴ ከፀሐፊው ጋር ተጋግዘን ብንዘጋውስ የሚል ከራስ የመነጨ ፍላጎት ጎነተለኝ።

የዛሬን አያድርገውና ድሮ በደጉ ዘመን የደብዳቤ ሚስጢራዊነቱ የተጠበቀ ነበር። የዕድሜ ባለፀጋ ሆነንም ሚስጢር የባቄላ ወፍጮ የሆነበት ዘመን ደረስን። እርስዎም ኢንጂነር ኃይሉን ፍለጋ ያባከኑት ኃይል፣ ገንዘብ፣ ጊዜና ሥልት አደባባይ ተሰጣጣ። በእርግጥ በአካል አግኝቼዎት አላውቅም። የማውቅዎት ኢትዮጵያን በሚመለከት በሚያቀርቡት ጽሑፎችዎ ቢሆንም፤ በሚያዚያ 24 ደብዳቤዎ ይዘት ግን የማውቅዎት የፍራንክፈርቱን አቶ ጌታቸውን ሊሆኑልኝ አልቻሉም።

የዘመኑ ይሉኝታ ቢስ የእነ ብርሃኑ ነጋ "ሲያዩት ሊሥቅ፤ ሳያዩት ሊሠርቅ" ምልምል ጮሌዎች ስብስብ ንፁሃን ታዋቂ ዜጎችን በተለያየ ስልት ከመጥለፍና ከማሣሣት አልፎ በሥሞቻቸው ጭምር እንደሚነግዱ፤ የኢትዮጵያን ፖለቲካ በቅርበት የሚከታተሉ ሁሉ ይረዱታል። መቼም ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው እንዲሉ፤ የእርስዎን ለተወሰነ ወቅት ከ"ሳይበር" መራቅ የተገነዘበ ግለሰብ ደብዳቤውን በሥምዎ ጽፎ ይሆናል የሚል የሃሳብ ብልጭታም ሞገተኝ። በሌላ በኩልም ደብዳቤው "የእነ ቅሌት በቁና ቡድን" ወያኔያዊ ተልዕኮውን ለማሳካት ላቀደው የማደናገርያ የትጥቅ ትግል፤ አብሪ ጥይቱን ማስቀደሙ ሊሆን ይችላል ብዬ አሰብኩ። ሆኖም በወቅቱ አስተያየት ከመስጠት ታቅቤ ሁኔታውን በመከታተል፤ በተገቢው ጊዜና ሁኔታ በጉዳዩ ዙሪያ የሚንከባለለውን ሽፍን ሴራ በአደባባይ ልሞግት መረጥኩ። በጽሑፌም ላይ የምጠቅሰው የደብዳቤውን ትክክለኛ ፀሐፊ እንጂ ዕውኑን አቶ ጌታቸውን እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል።

"ፓትሪዎት" ከሚባሉትና በፈታኝና ክፉ ወቅት በአንድነቱ ኃይል ላይ የተቃጣውን የባንዳዎችና የወያኔን ጥምር ዘመቻ መክተው የኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንን ጥቅም በአሸናፊነት ባስከበሩ ድረገፆች ላይ የኢንጂነር ኃይሉ ዉሎና የትግል እንቅስቃሴ አሻራዎች እሳቸው በሚመሩት "ቅንጅት" ደጋፊዎች፣ የቁርጥ ቀን ልጆችና የሕዝብ ታማኝ እንደራሴዎች ተሳትፎ ደምቆና በልዩ ማህደር በፈርጅ በፈርጁ ተጠርዘው ይገኛሉ። "ከአንጀት ካለቀሱ እንባ አይገድም" እንደሚባለው በእርግጥ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን ማግኘት ከፈለጉ፤ ያውም የአንደኛው አለም የመረጃ ፈሰስ ተጠቃሚ ከሆነ ግለሰብ፤ ዕውነታውን ከጽሑፍ፣ ከአውዲዮና ቪዲዮ ቅጂዎች እንዲሁም ግልጽ ውይይት በተደረገባቸው መድረኮች ሁሉ በመሳተፍ ብዙም ሳይወጣና ሳይወርድ በቀላሉ የልብን ማድረስ ይቻላል። እንዲያውም ለፋሲካ ዋዜማ ኢንጂነሩ ከዶ/ር ታዬ ወልደሰማያት ጋር በአሲምባ የፓልቶክ የውይይት መድረክ በመገኘት ከመላው ዓለም በኢንተርኔት ከሚከታተላቸው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ጋር ግልጽ ውይይት አድርገዋል። በኒውዮርክ ከታዋቂ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎችና ምሁራን ጋር ውይይት ባደረጉበት ስብሰባና ለእሳቸው ክብር በዋሺንግተን ዲሲ የመሸኛ ግብዣ ሊደረግ በታቀደበት ሰሞን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ በዝግጅት ላይ የመሆናቸው ዜና ሲናፈስ የእርስዎ ደብዳቤ በሕዋ ላይ መበተኑ ያስነጥሳል።

ውሎዎ በባንዳዎቹ ድረገፆች ላይ ሆኖ ከዛ በተቀዳ የአፃፃፍ ስልት ይሁን ወይም በማወቅ ሆን ብለው፣ አልያም ኃላፊነት በጎደለው ቸልተኝነት በፃፉት ደብዳቤዎ ውስጥ የተካተቱት ሐረጎች በወያኔና ሻቢያ ብብት ሥር አድገው በድንቁርናቸው የተቃኙና በውስጣችን የተተከሉ ባንዳ መዥገሮች፤ የእነ አንዳርጋቸው ፅጌ፣ የብርሃኑ ነጋ፣ የብርሃነ መዋና የጀርባ አጋሮቻቸው "የፎረም ሰማንያ አራት" ካድሬዎችን የሚያቀነቅኑትን ከንቱ ውዳሴ ነው ያስታወሱኝ።

ኢትዮጵያውያን በሺህ አመታት ታሪካችን ያካበትነውና የምንተዳደርበት "ማህበረሰባዊ ዕሴት" አለን። የዚህ አኩሪ ዕሴታችን ገደቡ ሲጣስ ደግሞ ማህበረሰቡ ኢትዮጵያዊ ገጽታውን እንዲጠብቅ፤ የሚያስተካክልበት ሥልት እንደ ሁኔታው ይለያይ እንጂ ዳብሮ ይገኛል። ሆኖም ሚያዚያ 24 ቀን 2000 አ/ም በእርስዎ ስም በተፃፈው ደብዳቤ ላይ የተካተቱት ጉዳዮች በአገር ውስጥ የሚኖረውንም ሆነ በውጭ አገር ያለውን ኢትዮጵያዊ ሕልውና የሚፈታተኑ እንዲሁም የሃገራችንን ማህበራዊና ፖለቲካዊ አስተሳሰብን በትክክል የማያንፀባርቁ፣ ሂደቱን ያዛቡና አንባቢውን ለማደናገር የተወጠኑ መታለፍ የሌለባቸው ጉድፎች ስላሉት፤ ነቅሰን በማውጣት በእርጋታ በጋራ አብረን እንድንመረምር፣ እንድንማማርና እንድናስተካክል በቅን መንፈስ እራስዎን እንዲያዘጋጁ እጠይቆታለሁ።

ጉዳዩ አንዴ አደባባይ ወጥቷልና በዚህ አጋጣሚ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ፈጣኑና ትኩሱ ትውልድ ከዚህ የሚቀስመውን በሕሊናው አዳውሮ፤ በሚፅፈውና በሚናገረው የተገራ የፖለቲካ ቋንቋ፤ የሃገሩ ጠላት ላይ በሚገባ እንዲያነጣጥር ብሎም የሕዝቡን ሚናና ያገኘውን ድል ጠንቅቆ በመረዳት ክብሩን ለማስጠብቅ እንዲተጋ ግንዛቤ የማስጨበጥ ታሪካዊ ኃላፊነታችንንም እንወጣለን።

**በዚሁ መሠረት፤**

1. በመጀመርያው ፓራግራፍ ላይ፤ "... 80 ሚሊዮን ሕዝብ መውጫና መግቢያ አጥቶ ሲንከራተት... ተቃዋሚ ቡድኖች ካይስማሙ ስለተስማሙ በሕብረትና በአንድነት ለመስራት ባለመቻላቸው መሳቂያና መሳለቂያ ሆነው ስለቀሩ... እርስዎና የትግል ጓደኞችዎ ሕዝቡን አሰባስባችሁ 6 ወር ባልሞላ ጊዜ... ተደራጅቶ ከመወያየት አልፎ በታሪኩ ታይቶ የማይታውቅ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረጉ በጣም ደስ ብሎታል።"... ብለዋል።

በዚህ አባባልዎ በተጠቀሙት ቋንቋና ገለፃ ሕዝባችን በዓለም ላይ ከሚኖር ማንኛውም ፍጡር የተለየ የሰማይ ቁጣ ወርዶበት ምድር ቀውጢ ሆና ሁነቱን መቋቋም ተስኖት ሲታመሥ በነፍስ የተደረሰለት አሥመሥለው የወያኔ ሰርጎገብ የሆኑትን የእነ ብርሃኑ ነጋን አለሌ የባንዳ መንጋ የ6 ወር የብተና ተውኔት ከመኳል ከኢንጂነሩ ጋር በጓደኝነት አዳብለው ለማቅረብ ሞክረዋል። ሕዝቡ ወያኔ የሙጥኝ ብሎ እንደ ቋንጣ ከደረቀበት የሥልጣን ኮርቻ ለማውረድ ያደረገውን ሥር ነቀል የሚያዚያ 30 ቀን 1997 አ/ም ሰላማዊ እንቅስቃሴ፤ የሰላማዊ ሰልፍ እርካታውን ሊወጣ እንዳደረገው ለማንኳሰስ መንፏቀቅዎ ለምን ይሆን?

እርስዎ ሊሉት እንደፈለጉት 80 ሚሊዮኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ መውጫና መግቢያ አጥቶ አልተንከራተተም። ህዝቡ እግዚአብሔር ባርኮ በሰጠው ሃገረ ኢትዮጵያ እንደየ ዕምነቱ ለአምላኩ እየፀለየ፣ እንደየ ኑሮ ደረጃው ማህበራዊ ዕሴቱን ተንከባክቦ የዕለት ከዕለት ሕይወቱን በመምራት አንድነቱን ጠብቆ እየኖረ ይገኛል።

ከቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም ጋር ተያይዞ በወቅቱ በአለማችን በተከሰተው የኃይል ሚዛን መዛባት የተፈጠረው አጋጣሚ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ሕልውና ላይ ያነጣጠረ ከፍተኛ አደጋ ነበር። ሆኖም እ.አ.አ በግንቦት 1991 ዓ/ም አለም ሲተነብይልን የነበረው እንደ ዩጎዝላቪያ፣ ሩዋንዳና ሶማሊያ የእርስ በርስ ዕልቂትና በትናንሽ ግዛት ተሸራርፎ ሕልውናን የማጣት ሟርት መክኗል። ይህ እርስዎ አዛብተው ሊነግሩን እንደዳዱት መውጫ መግቢያ ያጣው ሕዝቡ ሳይሆን፤ በኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች መጠነ ሰፊ ዕርዳታ፣ በነፍጥ ኃይልና በተለይ በአሜሪካና በእንግሊዝ የሥለላ ድርጅቶች ቡራኬ ያለ ኢትዮጵያውያን ይሁንታ በሕዝባችን ጫንቃ ላይ የተንጠላጠሉት የጥፋት መልዕክተኞች ሻቢያ፣ ወያኔ፣ ኦነግና ደንገጡሮቻቸው ናቸው መሳቂያና መሳለቂያ የሆኑት። በሕዝብ ትግል ስም ሲነግዱ የነበርና በቅርቡ የአቶ መርሻን ዱካ ተከትለው ከኢህአፓ በማፈንገጥ የወያኔን ዕድሜ ለመቀጠል ያደቡ ጥቂት አደግዳጊዎች ናቸው መሳቂያና ማፈርያዎች። በተለይ ባረጀ ባፈጀ የወያኔ/ሻቢያ ስልት፤ በአሳዳጊዎቹና በቀጣሪዎቹ አይዞ ባይነት ሕዝብን ግራ ለማጋባት ሰሞኑን "የግንቦት 7 (የግም ሞት) የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ" በማለት እራሱን የሚጠራውና ከሥረ መሠረቱ የምናውቀው የባንዳ ፎረም 84 ቡድን ነው መሣቂያ መሣለቂያ የሆነው።

<u>ይህ ቡድን የማጭበርበር ምትሃቱ መክኖ ዕርቃኑን በመቅረቱ በድርጅቱ መርሃ ግብር መግቢያው ላይ</u> "... የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተገዢነት አልፎ በዜግነት ደረጃ የታየበት አንድም ጊዜ የለም" <u>በማለት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥላላት በእምብርክክ እየዳኸ የክህደት እሪታውን በማቅለጥ ላይ ይገኛል።</u> በቅርቡም ጁን 8 ቀን 2008 ዓ/ም በእንግሊዝ፤ ለንደን ላይ አንዳርጋቸው ፅጌና ጥቂት ግብረአበሮቹ በቅንጅት ሥም ለብርሃኑ ነጋ ባዘጋጁት ስብሰባ በይሉኝታ፣ በስብዕናና ግብረገብ እንዲሁም በሠለጠነ የፖለቲካ አመራር ሂደት ላይ ኪሣራን በአደባባይ አውጀዋል። ለዚህ ድርጊት በአባሪ ተባባሪነት ከስቶክሆልም ስዊድን ብቅ ያለው ፈጥኖ ደራሽ ነው ይበልጡን የቀለለውና የተጋለጠው። አዎ "በልጅ አመካኝቶ ይበሏል አንጉቶ" እንደሚባለው "ልደቱን" የመሰለ ከሃዲ አሰልጥኖ ያልሆነለት፤ የመጨረሻ ዕድሉን በብርሃኑ ነጋ አኪር ሊሞክር ወይስ ደበበ እሸቱን ካስጎመጀችው የሲአይኤ 20 ሚሊዮን ዶላር ለመቀላወጥ? እኚሁ የስቶክሆልም "የምንትስ ቦርድ ሊቀመንበር" ብለው እራሳቸውን ያስተዋወቁት ዶ/ር አድማሱ ገበየሁ፤ የቅንጅት ሊቀመንበር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ድርጁቱን ከጥቃት ለመከላከል ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ/ም በቅንጅት ካዕላይ ምክር ቤት እስኪወስን በእነ ብርሃኑ ላይ ለወሰዱት እርምጃ የፃፉትን ጊዜያዊ "የእገዳ ደብዳቤ" ፅንስ አጣመው በማቅረብ፤ ሊቀመንበሩ ግለሰቦቹን በደብዳቤ እንዳባረሩ አድርገው በአደባባይ ሲናገሩ የተባለው "የቅሌት ተስቦ" እንደለከፋቸው ተገነዘብኩ። "የአይጥ ምሥክር ድንቢጥ" ይሏል እንዲህ ነው። በስዊድን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አንበሶች ዶክተሩን ከሚመለከት የቤት ሥራቸው ጥቂቱን ሥበልት አጨራረሱን እንደሚያወዙት እተማመናለሁ።

ለመሆኑ በለንደን የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ ድርጅት ነን ብለው ለብርሃኑ ነጋ፣ አንዳርጋቸውና መሰሪ ተግባራቸው በግምባር ቀደምትነት በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ላይ ጁን 8 ቀን 2008 ዓ/ም ለተካሄደው የፌዝ ፖለቲካ ድራማ የመድረክ መጋረጃ ገላጭ ተለጣፊዎች ምንኛ ፈጣጣ ሃፍረተቢሶች ናቸው! እግዚዖ ያሰኛል። "ዝንጀሮ በሰው ክምር ልጅዋን ትድር" እንደሚባለው፤ ብርሃኑ ነጋ የሠርጎ ገብነት ተልዕኮውን በሌላ መልክ ለመቀጠል ከቅንጅት እራሱን እንዳገለለ ገልፆ ከአንዳርጋቸው ፅጌ ጋር ሌላ ድርጅት መመሥረቱን ባወጀ በወሩ እንደገና በቅንጅት ሥም እንደ ቅንጅት ከፍተኛ አመራር ቀርቧል። በለንደን ስብሰባ ላይ በቅንጅቱ ሊቀመንበር ላይ ባልተገራ ምላሱ አሉባልታውን ከመንዛቱ ባሻገር። በወያኔና በሻቢያ ከጥንቱ የሰለጠነበትን በአንድ ብሄረሰብ፤ በአማራው ላይ ያነጣጠረ የጅምላ የጥላቻ ዘመቻውንም በዚሁ ዕለት አያይዞ ይፋ አድርጓል። ወያኔ እ.አ.አ በ1991 ዓ/ም ለንደን ላይ በተጠነሰሰ ሤራ ያለ ሕዝብ ይሁንታ የሥልጣን እርካቡን እንዲቆናጠጥ ሲደረግ፤ አንዳርጋቸው ፅጌም በዚያው ዘመን ከለንደን ወያኔን ተከትሎ በመግባት በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ የታወጀውን የማፍረስ ዘመቻ በአጋፋሪነት ሲያስፈፅም ከርሞ አሁን ደግሞ በሠርጎገብነት ለተያያዘው ሌላኛው ዙር ዘመቻ ሲንደፋደፍ፤ የበይ ተመልካች ሆኖ በመሃል ሰፋሪነት መጃጃል ከጠላት ጋር

እንደማበር ያስቆጥራል። በአጠቃላይ በእንግሊዝ አገር የሚኖሩ ዕውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች በዚህ ቡድን ላይ የወሰዱት አቋም የሚያኮራ ቢሆንም ፈጣን እርምጃቸው ይጠበቃል።

እ.አ.አ በግንቦት 1991 አ/ም መጨረሻ ላይ ለህትመት በበቃው የታይምስ መጽሔት ላይ "በኢትዮጵያ ዋና ከተማ በአዲስ አበባ ሕዝቡ አማፂዎቹን እንደ ወራሪ ጦር በመመልከት ምንም አይነት አቀባበል አላደረገም.." ብሎ አስፍሯል። በወያኔ ሳንባ የሚተነፍሱ ባልተኞች ሊነግሩን እንደሚሞክሩት ሳይሆን፤ ብዙሃኑ በአገር ውስጥ ያለ ሕዝብ የሻቢያና ወያኔን መሰሪ ተንኮል ጠንቅቆ ተረድቶት ስለነበር በእታሞና በዘንባባ ዝንጣፊ አልተቀበላቸውም። እንደ ወቅቱ የአለም ተጨባጭ ሁኔታ እነሱው በመረጡት የትግል ስልት ነው ግብግብ የገጠማቸው። ታዲያ እርስዎ "የወያኔ ግሎኮስ" የሆኑት ከሃዲና ባንዳዎቹ ከጅብ ቆዳ በተሰራ ከበሮ የሚደልቁትን እንደ ገደል ማሚቶ ከማስተጋባት በቀር በምን መሥፈርትዎ የሕዝብ ወገን የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶችን "መሳቂያ መሳለቂያ" እንዳሉ በቂ ምክንያት ማቅረብ እንደማይችሉ ከአያያዝዎ መረዳት ይቻላል።

ገበሬው፣ ሠራተኛው፣ የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኛ፣ አስተማሪው፣ ተማሪው፣ የኪነ ጥበብና የሥነ ጥበብ ባለሞያው፣ ወጣቱ፣ ሴቱ፤ ሁሉም በተደራጀበት ማህበርና የሥራ መስክ ማህተቡን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በማድረግ፤ ወያኔና ሻቢያ በቀላሉ ሊንዱት ያቀዱት የኢትዮጵያዊነት መንፈስ፤ በጽኑ መሠረት ላይ የተገነባ የማይነቃነቅ ዋልታ እንደሆነ በገሃድ አስመስክረዋል። ለዚህም ሲባል ባለፉት 17 መራራ የትግል አመታት ሕዝባችን በገንዘብ የማይተመን እጅግ ውድ ዋጋን ከፍሎበታል። ስለዚህ የሕዝብ ብሶትና ትግል የወለዳቸውን፤ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልና በአሁኑ ወቅት አሳቸው ከሚመሩት ቅንጅት ጋር በፅናት በቆሙት ታማኝ የአመራር አካላትና አባላት ታዛ ሥር የወያኔን ሰርጎገቦች እንደ ትግል ጓዶች ለማስጠለል እንደ ካሥቲክ መሳብዎ ትዝብት ላይ ጥሎዎታል። እስቲ ወረድ ብለን የደብዳቤዎን ቀጣይ ገፅታ እንዳብስ

2. በሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ፤ "...በውጭ አገር የሚኖሩ ወገኖቻችሁን ለመጎብኘት ወደ አሜሪካ ስትመጡ... በመካከላችሁ አለመግባባት ተፈጠረ፣ የተበደለ ተክሶ፣ ያጠፋ ተወቅሶ እርቅ እንዲደረግ ቢሞከር ስላልተቻለ...." በማለት ከእሥር የተፈቱት የወቅቱ የቅንጅት አመራር አባላት ወደ ውጭ ያደረጉትን ጉዞና ዕርቁን በሚመለከት እውነታውን ሊያዛቡ ሞክረዋል። ሆኖም ሁነቱ የቅርብ ጊዜ ትዝታ በመሆኑ በመረጃነት በሚገባ ተጠናቅሮ በመልክ በመልኩ በማይፋቅ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ ሰፍሯል። እርስዎም በሽምግልና ሰበብ በጓሮ በኩል በእጅ ጥምዘዛው ተሰማርተው ሰሚ በማጣትዎ በዚህች ደብዳቤ ሰበብ በኢንተርኔት ሎሎታዎን ለማቅለጥ አምጠው የፈጠሩት መላ ለመሆኑ፤ "ሻርለክ ሆምስ" አፈር ይቅለለውና ጉዳዩን እንዲያጣራ ነፍሱን ዕረፍት ነስተን አንልክብዎትም።
በዚህ ብቻም አልተወሰኑም ቀጥለውም ". . . የእናንተ ከአገር መውጣት ለመለስ ታላቅ ዕረፍት ስለሰጠው... በጎንደር ያለውን መሬት ለሱዳን ሸጠ።" ብለው ቁጭትዎን ይሁን በውስጠ ወይራ ኢንጂነሩን ለመወንጀል የመዘዙት ሐረግ የጥንቱን የንባብ መጽሐፍ አስታወሰኝ። የተንኮለኛው ከበደን "የአሁኑ ይባስን"። ታዲያ እርስዎ መለስ ዜናዊን በዚህ መልኩ ከሣሉት፤ ፈሪሃ እግዚአብሔር አድሮበታል ማለትዎ ነው? እንደዛማ ከሆነ ምን አስጨነቀዎ! የኢንጂነሩን ዱካ ተከትሎ የሸጠውን መሬት እሳቸው ሲመለሱ የገባበት ገብቶ ከነወለዱ ያመጣታል። ለነገሩ ለራስዎ ግራ ተጋብተው ሌላውን ግራ ለማግባት መጣደፍዎ ምን ትርፍ ያስገኝልዎት እንደሆን እራስዎ ያሥሉት።

የወያኔ ቁንጮ አቶ መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቻቸው ከሕዝብ ይሁንታ ውጭ በነፍጥ ኃይል ሥልጣን ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያና በሕዝብዋ ላይ ከፍተኛ ክህደት በመፈጸም ብሔራዊ ጥቅማችንን አሳልፈው ሰጥተዋል። የእነሱን ሤራ በመቃወም በሰላማዊ ትግል ተቃውሚቸውን ባሳዩ ንፁሃን ዜጎች ላይ ጭካኔ የተሞላበት ወንጀል ፈጽመዋል። የኢትዮጵያን የግዛት ሉዓላዊነትን አስመልክቶ የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ፣ በግል፣ በመንግሥት ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ የሚያደርገው ማንኛውም ስምምነት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የለውም። በአሁኑም ወቅት በሃገር ውስጥና በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ይህንን በመቃወም ቁጣውን እያሳየ ይገኛል። የጥቃቱ ሰለባ ከሆነውና ከተፈናቀለው ኢትዮጵያዊ ወገናችን ጎንም በጽናት እንቆማለን።

3. በሦሥተኛው ፓራግራፍ ላይ፤ ከጅምሩ "... ይህን ግልጽ ደብዳቤ ለመፃፍ የተገደድኩት ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን በፋክስ፣ በስልክ፣ በኢሜይል ለማግኘት ሞክሬ ስለአቃተኝ በኢንተርኔት ሙከራ ለማድረግ ነው።..." ብለዋል። በአንድ የፓልቶክ ክፍል ውስጥም ከአውሮጳ በእርስዎ ምካስ የሚያካምጥ ጉደኛ ደብዳቤውን እያነበነበ የቆጥ የባጡን እየዘላበደ ኢንጂነሩን ሥራ ሊያስፈታ የሞከረ ግለሰብንም ታዝበናል። መቼም ይህ ሁሉ ጭንቀትና ጥበት ለነገው ቤታችን ለመንግሥተ ሰማያቱ ቢሆን፤ "ታምሜ መች ጠየቃችሁኝ? ተርቤ መችስ አበላችሁን? ተጠምቼ መችስ አጠጣችሁኝ? ታርዤ መችስ አለበሳችሁኝ? ወዘተ..." መልሥ በሚገባ ተሰናድተዋል፣ አይተናል ብለን በሺህዎች የምንቆጠር እንመሰክርልዎታለን። (ከዛኛው አለም መዝገብ ቤት ላይ በአጋጣሚ ስይፃፍ ቢዘነጋ ለምስክርነት መጠራታችን አይቀር)። ለእኔ ይህ ጉዳይ የጤና ሳይሆን ከእነ እትዬ ብርቱካንና ጋሽ ብርሃኑ ሠፈር በገል የተጫረ ረመጥን ለመቆስቆስ የታለመ ነው የመሰለኝ።

በዋሺንግተን አየር ማረፊያ ከሕዝብ ጋር በጋራ ሆና መሪዋን፣ የትግል አጋርዋን፣ ሕመምተኛውን አዛውንት ለመቀበልና ለማየት ፈቃደኛ ያልሆነች ዘመናይ ፈጣጣ ባንዳ ወ/ሮ ብርቱካን .... በብርሃኑ ነጋ አጋፋሪነት በተገኘው ቦታና አጋጣሚ ሁሉ "ጋሽ ኃይሉን ፈልጌ አስፈልጌ አጣሁ..." በማለት ሕዝብን ግራ አጋብታ ኢንጂነሩንና አጋሮቻቸውን

በማሳጣት ወያኔያዊ ተልዕኮዋን ለማሟካት ሞክራ ነበር። እርስዋም ቅጂውን ልክ እንደስዋ በደብዳቤዎ ሊገልጹ መፈለግዋ አይገርመንም።

ታዲያ ከላይ የጠቀሱትን የመገናኛ ዘዴዎች ተጠቅመው ልብዎ እስኪትወልቅ ኢንጂነሩን በፍለጋ የደከሙበትንና መልስ ያጡበትን አንዱንም አድራሻ ለምን ሊጠቅሱ አልቻሉም? የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዲሞክራሲ፣ ለሠላም፣ ለዕድገትና የህግ የበላይነት የሰፈነበትን ሥርዓት ለመመሥረት የሚያደርገውን እንቅስቃሴና ትግል ለማዳፈን በጥቅምና በቁራሽ ሥልጣን ድለላ የታወሩ ጥቂት ይሉኝታ ቢሶችና ግብረአበሮቻቸው ሰሜን አሜሪካን እንደ መስፈንጠርያ ወለል ለመጠቀም ከአገርቤት ተጣድፈው እንደወጡ ሳይውል ሳያድር ነበር ነውርና ትክክለኛ ባህሪያቸው አደባባይ የወጣው። በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ የተቃጣውን ይህንኑ ሥውር ደባ ሰብሮ ለመውጣት በተደረገው ትግል ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ወሳኝና ታሪካዊ ሚና ተጫውተዋል። በውጭ አገር ያለው ኢትዮጵያዊም ወያኔ በሕዝብ ትግል ውስጥ አሰርጎ በማስገባት በተከላቸው መሰሪ ባንዳዎች ተወናብዶ የሕዝቡን ትግልና ድል ለወያኔ ጫማ መረማመጃ ንጣፍ ለማድረግ ለሚቅበዘበዙት እንዳይበገር፤ ከሕመማቸው ሳያገግሙ በተሽከርካሪ ወንበርና በከዘራ ደጋፍ በተለያዩ ከተማዎች እየተዘዋወሩ እውነታውን በአደባባይ ሲገልጹ ከሕዝብም ለሚቀርብላቸው ጥያቄ መልስ በመስጠት የአንድነቱን ጎራ አጠናክረዋል። ከደረሰባቸውም ከፍተኛ ሕመም በሕክምና ለመረዳት በሆስፒታል ገብተው ሲታከሙ ቆይተዋል። እርስዎም ሁሉም ነገር ተጠናቆ፣ ኢንጂነሩም ድነው ቀጣዩን ውስብስብና እልህ አስጨራሽ ትግል ለመምራት፤ የተዛባውን የአንድነቱን ጎራ የኃይል ሚዛን በማስተካከል ወደ ድል የሚወስደውን ጎዳና ለማጽዳት ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ዝግጅት ባደረጉበት ወቅት ደብዳቤውን መፃፍዎ፤ የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታ አብጠርጥረው በሚያውቁና በሚከታተሉ ወገኖች ዕይታ ለስውር ተልዕኮዎ የመጨረሻዋን ድንጋይ በመወርወር ድርሻዎን እንደተወጡ ያስቆጥራል።

<u>4. የደብዳቤው ፀሐፊ በአራተኛው ፓራግራፍ ላይ</u> ኢንጂነር ኃይሉ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ምን እንደሚጠብቃቸው "በዲግላ ድመቶቹ" የምናብ ወፍጮ የላመውን ቅዠት በሕዋ ላይ ሲበትኑ እንዲህ ይላሉ፤ ". . . . በድምፅዎ መጥፋት ብዙዎች ተስፋ በመቁረጥ ወደ ጠላት ጎራ ገብተዋል፣ ግማሹም ደካማ ስለሆነ ወያኔ ገዝቶት ሰላይ መሆን ተገዷል።" . . . .አቶ ጌታቸው እዚህጋ እንደ ሰሞነኞቹ ፈጣጣ የፖለቲካ አራዳዎች በጣምም አይፍጠኑ። የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ወገን የሆኑ ሁሉ የትግል ቃልኪዳናቸውን በማደስ በአቋማቸው ፀንተው ተስፋ ለቆረጠው አርዓያ በመሆን ለቀጣዩ መራራና ውስብስብ ትግል በአዲስ መንፈስና ስልት እራሳቸውን አዘጋጅተዋል። በተለያዩ የኢትዮጵያ ወረዳዎችና ዞኖችም የተዘጋውን የቅንጅት ጽ/ቤት በመክፈት ሕዝብን አሰባስበው ነው መሪያቸውን ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን የጠበቁት። እሳቸውም በውጭ አገር ቆይታቸው ዘመኑ ባፈራው ጥበብ ተጠቅመው አገር ውስጥ ካሉት የቅንጅት አመራር አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር በውስጥና በውጭ በሕዝብ ትግልና ድል ላይ የተዶለተውን ሤራ ለማምከን ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።

ሕዝባችንም ሆነ ከአብራኩ የወጡ ሐቀኛ ልጆቹ በሚያዚያ 30 ቀን 1997 ዓ/ም ታሪካዊ የድጋፍ ሰልፍ. . . . "**ትላንት ለቲሸርት. . . ዛሬ ለሃገሬና ለመብት**" . . .በማለት በአደባባይ ያሳዩትን ትዕይንት በምርጫ ሣጥን ውስጥ በመድገም በሥነ ምግባር ጨዋነት የበላይነታቸውን አስመስክረዋል። እርስዎ በደብዳቤዎ ላይ እንደጠቀሱት ከዕውነተኛ የሕዝብ ወገን ሕልውናውን ሸጦ ለወያኔ ያደረ ገልቱ የለም። በእርግጥ ከድሮው የወያኔና የሻቢያን ጡት ጠብተው በማደግ ለ 15 አመታት ያህል የወያኔ ምላሥና ሣንባ ሆነው ያገለገሉ ታማኝ ባንዳዎች በ1997 ምርጫ ሳቢያ በወያኔ መሠሪ ተንኮል በህዝባዊ ትግሉ ውስጥ ሠርገው በመግባት የድሉን ውጤት ፍሬ ለጠላት አሳልፈው የሰጡት እነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በጣት ከሚቆጠሩ እበላ ባይ ከሃዲዎች ጋር ከኢህአፓ ያፈነገጡ ጥቂት አስመሳዮችን አስከትለው ወደ ወያኔ ጎራ አቅንተዋል። "**የቁማርን ለቁማር**" እንደተባለው ነውና ድርጊቱ አይገርመንም። እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት አንድ ጉዳይ ቢኖር በአሜሪካን ድምፅ ራዲዮ ወስጥ የመሸጉት የፎረም 84 ካድሬዎችና ንኪኪዎቻቸው እንዲሁም የጀርመን ራዲዮው የዋሽንግተን ወኪል "ለግም ሞት ስባት የፖለቲካ ንቅናቄ" ቱባ ዲግላውና መሰሎቻቸው እያቃሰቱ የሚሰጡትን የአየር ሽፋን የኢትዮጵያ ሕዝብ በትዝብት እየተከታተለው መሆኑን ማስገንዘቡ ተገቢ ይመስለኛል። እስቲ ደግሞ በጉደኛ ደብዳቤዎ የታየውን ተውኔት የመጨረሻ ክፍል የመድረክ መጋረጃ እንግለጥ፤

<u>5. አቶ ጌታቸው በደብዳቤያቸው መደምደሚያ</u> በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ሲወቅሱና ሲዘልፉ፤ እንዲሁም ሃገር ውስጥ የቀሩትን ምሁራን ሲተቹ ". . . ኢትዮጵያ ብዙ ልጆች ወልዳ የወላድ መካን ስለሆነች ምሁራን የሚባሉት አዋቂዎችዋ ተፀይፈዋት ሲሸሹ አንድ ቀን የድል አጥቢያ አርበኞች ሆነው መምጣታቸው አይቀርም፤ የቀሩትም መለስ ዜናዊ ክንድ ላይ ተንጠልጥለው ጠዋትና ማታ ያለ ዕረፍት እየጠቧት ነው" ይላሉ። ፀሐፊው እነማንን አንገት ለማስደፋት አምጠው የመዘዙት ሐረግ ይሆን? የምሁርነት መስፈርቱ በእርስዎ ምናብ እንዴት ይሰላል? ማንን ይጨምራል ማንንስ ያገላል? በዚህ ጉዳይ ላይ በስሜት ወይም በማን አለብኝነት ተነሳስተው የጅምላ ውንጀላ ዶፍ ካማውረድዎ በቀር ለእኔም ይሁን ለአንባቢዎች የሚሰጡት አንዳችም አጥጋቢ ማብራሪያ እንደሌለዎት "**የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል**" የሚሉት ብህል ያጤኗል።

እናት ኢትዮጵያ የወላድ መካን አይደለችም። "**የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ነው**" እንደሚባለው ሁሉ በመልክ፣ በባህርይ፣ በአካላዊ ቅርፅ ወዘተ. . . ልዩነት የሚታይባቸው ልጆችን እናት ታፈራለች። በሃገራችንም ያለው ነባራዊ ሁኔታ ከዚህ አይዘልም። በኢትዮጵያችን ፈሪሃ እግዚአብሄር ያደረባቸው ለሃገርና ለወገን ቅን፣ ታዛዥና ታማኝ የሆኑ ዜጎች ተወልደዋል፤ አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ግዴታቸውን ተወጥተው ታሪክ ሰርተው ያለፉ የስመጥር ዜጎች ባለሃብትም ነን።

አሁንም የአያት ቅድመ አያቶቻቸው ኢትዮጵያዊ ስነ ምግባርና መንፈስ የተዋሃዳቸው ቁም ነገረኞች፣ ታሪክ የሰሩና ለመስራት የሚጣደፉ ብዙሃንን አፍርተናል። ታዲያ ከስንዴ መሃል እንደሚለቀም እንክርዳድ በጣት የሚቆጠሩ ባለጊዜ ባንዳዎችና ከሃዲዎች በቅለው ከፈጠሩት ድርጊት ምሁሩ በጅምላ የሚኮነንበት ምክንያት **"አህያውን ፈርቶ ዳውላውን"** ካልሆነ በቀር ካቀረቡት ከበጣ ሌላ የሚያፈናፍን መውጫ የሎትም።

ፀሐፊው ያልተረዱት አንድ ነገር ቢኖር እናት ኢትዮጵያን እንኳን ከአብራክዋ የወጡ ልጆችዋ ይቅርና ጠላቶችዋም በግዳጅ ተገፍተው መባረራቸው እንጂ ተጠይፈዋት የሸሹበት ጊዜ የለም፡፡ ከአገሩ የወጣ ዕውነተኛ ኢትዮጵያዊ በአካሉ እንጂ ሁለመናው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። በፈታኝ የመከራ ወቅትም ከእራሱም አልፎ የሚኖርበትን አገር ሕዝብና መንግሥት አስተባብሮ ከኢትዮጵያ ጎን በመቆም ማንነቱን አስመስክሯል። ኑዛዜውም **"ብሞት እሬሳዬን ለሃገሬ ምድር አብቁ ነው።"** በውጭ አገር ያሉ ኢትዮጵያውያን የግንቦት 1997 ምርጫን ተከትሎ በሃገራችን በተፈጠረው ውዝግብ፤ የሕዝብን ድምጽ ለማስከበር፣ የታሰሩትን ለማስፈታትና የወያኔ/ኢህአዴግ ታጣቂዎች በንጹሃን ዜጎች ላይ በአደባባይ የፈጸሙትን ኢሰብአዊ ድርጊትና ግድያ በመቃወም ብሎም ጥፋተኞችን ለፍርድ ለማቅረብ በተለያዩ ክፍለ አለማት በሚገኙ ታላላቅ ከተሞች ያደረጉት ሰላማዊ ሰልፍና የዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ ምን ያህል ሃያል እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ቢሆንም ቀንደኞዎቹ የወያኔ ሰርጎገብ የሆኑት አንዳርጋቸው ፅጌ፣ ብርሃነ መዋና ግብረ አበሮቻቸው ይህንኑ አጨናግፈው የወያኔ ባለሥልጣናትን ለማዳን የተጫወቱት ቆሻሻ የፖለቲካ ቁማር በቀትር ፀሐይ የጠወለገ የአደባባይ እንደሆኽላ ሆኖ በታሪክ መዝገብ ላይ ሰፍሯል።

እርስዎም ሁለመናዎ እስኪነቃቃ የጠፋን ሰው ለመፈለግ ዓለምን ባሰሱባት የማስመሰያ ደብዳቤዎ የጠላትን የምኞት እሪታ እንደ ገደል ማሚቶ አስተጋብተው፤ ሐገር ወዳዱ ዜጋ ላይ ለተከፈተው የሥነ ልቦና ዘመቻ የበኩልዎን አሉባልታ ለመንዛት ያደረጉትን ሙከራ ከንቱነት በመረጃ ለማጠናከር ኢንጂነሩ የኢትዮጵያን ምድር እስኪረግጡ መጠበቅ አስፈላጊ ነበር። ሕዝብ በዱላ ወይስ በአበባ እንደተቀበላቸው ተረድተው እርስዎ እራስዎ በገዛ ሥራዎ እንዲፀፀቱ ጊዜ ለመስጠት ብዕሬን ገታሁ። ሆኖም ቀጣዩ ትግል በተገራ የፖለቲካ አስተሳሰብና ቋንቋ እንዲመራ ፈሩን ለማስያዝ ዕውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች የሚያደርጉትን ያካሰለሰ ጥረት ለማጠናከር ወቅትና ጊዜውን ጠብቄ ብዕሬን ኮረኮርኩ።

አዎ ወቅትና ጊዜውን አልኩ! ነገሩ እራሴንም እየገረመኝ ያስቀኝ ገባ። ሰሞኑን በውጭ አገርና አገር ውስጥ ያሉ ከሃዲዎችና ባንዳዎች ምድር ቀውጢ ሆናባቸዋለች። የሥጋ ዘመዳሞቹ ብርሃኑና መርሻ በውጭ ያለነውን በሾኬ ለመጣል የጀመሩት ዱለታ እነሱኑ በእንብርክክ የኋልዮሽ እያስኬዳቸው ይገኛል። በአገር ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት የነሳቸው እነ ብርቱካን **"የሞኝ ልቅሶ መልሶ መካልሶ"** እንደሚባለው ነጋ ጠባ በየሥርቻው መሰብሰባቸውንና መመራረጣቸውን ሪፖርት በማቅረብና በማወናበድ ለማይጠረቃው የወያኔ የውሸት ቋት ታማኝ አጋርነታቸውን ጁን 18 ቀን 2008 ዓ/ም ከማረጋገጥ ያለፈ ሊያሳዩን የቻሉት ትንግርት የለም።

ኢንጂነር ኃይሉ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በሕዋላ በቅንጅት ውስጥ ሲታይ የነበረ መጠነኛ አለመረጋጋትን አስወግደዋል። ከፓርቲው አመራር አካላትና አባላት፣ ከታዋቂ ግለሰቦች፣ ከወጣቶችና ሴቶች ጋር በቅርቡ ያደረጉትም ውይይት የፓርቲው ሕልውና በጠንካራ መሠረት ላይ መገንባቱን ጠቋሚ ነው። ሰሞኑን በኢትዮጵያ መዲና የሚደረገው አገር አቀፍ የቅንጅት ጉባዔ ስኬታማ እንዲሆን በአገርና ውስጥና በውጭ አገር ያለ ዜጋ ልባዊ ምኞት ነው።

በእርግጥም የሃገርና የህዝብ ጠላቶች በወገን ላይ ያደረሱት ጥፋት በቀላሉ የሚወሳና የሚገለጽ ባይሆንም፤ አሁንም በጋመው የሕዝብ ትግል ውስጥ ሎሌዎቻቸውን አሠርገው በማስገባት በአልሞት ባይ ተጋዳይነት የአንድነት ኃይሉን የድል ጉዞ ለመግታት የሚፈፅሙት ደባ በግልፅ ይታያል። ሕዝቡ ይህን ተገንዝቦ በሐቀኛው የቅንጅት መሪ በኢንጂነር ኃይሉ ሻውልና እውነተኛ ልጆቹ ላይ ያለውን ከፍተኛ ዕምነት እሳቸው ወደ አገር ከተመለሱ በሕዋላ ዳግም ማሳየቱን በግልጽ መረዳት ተችሏል። የአንድነት ኃይሉ የፖለቲካ ድርጅቶችም ትግሉን ከሠርጎ ገቦችና አንጃዎች እያፀዱ፤ የኢትዮጵያና የሕዝቧን ብሄራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ከሚያደርጉት ሁለገብ እንቅስቃሴ ትይዩ ከአለም ሕብረተሰብ ጎን በመሰለፍ፤ ምድራችን ሰላም፣ ዲሞክራሲና የሕግ የበላይነት የሰፈነባት ምቹ የሰው ልጆች መኖርያ እንድትሆን አለም አቀፋዊ ግዴታቸውን እንደሚወጡ ከመቼውም በላይ በከፍተኛ ሞራል ተነስተዋል። በውጭ አገር የሚኖሩትም ኢትዮጵያውያን የባዕዳን ተልዕኮ አስፈፃሚ ምልምሎችን በየአደባባዩ እያጋለጡ አገር ቤት ካለው ትግል የጀርባ አጋርነታቸውን በማስመስከር ላይ ይገኛሉ።

የሰው ልጅ ፀጉሩ ሲከዳው በአነጋገሩ ቁጥብ፣ በአዕምሮው ብስል፣ ልቡም ብልህ ደግና ሠላም የነገሰባት ትሆናለች። ይህና መሰል የተፈጥሮ ህግጋት አይመለከተንም የሚሉ ዳንዴ ግብጣ አራዳዎችን ምርኩዝ እስኪያስተምራቸው አልፎ አልፎ በወግ የወዛ **"የዝምታ ለበቃችንን"** መዘን ኢትዮጵያዊ ሥርዓትን ማስተማር ተገቢ ይሆናል።
የደብዳቤው ፀሐፊም ሰንብቶ በሁሉም ምናብ ሲብሰለሰል የቆየ የአደባብይ ዶሴን ለመዝጋት በእርጋታ እስከ ደብዳቤው ፍፃሜ እንደሚዘልቁ አምናለሁ። በሚኖሩበት አገር ካሉ ዕውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች ጋር ሁነውም ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ፈጥነው በመራመድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋና ሙሉ ዕምነቱን ለጣለባቸው፤ በኢንጂነር ኃይሉ ሻውልና በዶ/ር ታዬ ወልደሰማያት ለሚመራው የአንድነት ኃይል በተግባር ሙሉ ድጋፍዎን ለመስጠት እንደሚተጉ ተስፋ አደርጋለሁ።

**ቸሩ እግዚአብሔር ኢትዮጵያና ሕዝቧን ይባርክ**